ሠላሳ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
34th Year — No. 26

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.
Addis Ababa, 29th April, 1975

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ።

NEGARIT GAZETA

የጋዜጣው ፡ ዋጋ ፤	በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይታተማል ።
ባገር ፡ ውስጥ ፡ ባመት ፡ $ 6		የፖስታ ሣጥን ቁጥር ፩ሺ፴፩ (1031)
» » በ፮ ፡ ወር ፡ $ 3		
» » ያንዱ ፡ $ ¼		

ማውጫ
፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፷፯ ዓ. ም.
የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ
የወጣ አዋጅ . . . . ገጽ ፺፫

CONTENTS
1975

Proclamation No. 31 of 1975
Public Ownership of Rural Lands
Proclamation . . . . Page 93

አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ

«ኢትዮጵያ ትቅደም»

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በእርሻ በሚተዳደሩ አገሮች አንድ ሰው በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው የኑሮ ደረጃ ፤ መብት እንዲሁም ክብርና ማዕረግ የሚወሰነው ከመሬት ጋር ባለው ግንኙነት በመሆኑ ፤

በአገሪቱ ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ጋሻ መሬት በጥቂት መሳፍንት ፤ መኳንንትና ባላባት ቤተሰቦች ተነጥቆ ስለ ተያዘ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጭሰኝነት እንዲያገለግል በመደረጉ ፤

ለብዙ ዓመታት ባላባታዊ ግፍና ጭቆና የተፈጸመበትን፤ በረኃብ ፤ በእርዛትና በበሽታ አለንጋ እየተገረፈ ለባላባታዊው መደብ ቅንጦት ፤ ብኩንነትና መንደላቀቅ በላቡና በደሙ የከፈለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለበት የጭቆና አገዛዝ እንዲላቀቅና ለኢትዮጵያውያን በሙሉ እውነተኛ እኩልነትን፤ ነፃነትንና ወንድማማችነትን ለመመሥረት ትክክለኛ መድኅን መሠረታዊ የመሬትና የእርሻ ይዞታ ለውጥ ማድረግ በመሆኑ ፤

የወደፊቷ ኢትዮጵያ ልማት የተረጋገጠ ዋስትና የሚኖረው አሁን እንዳለው ሁኔታ የአንዱ ብልጽግና ለብዙኃኑ መቆርቆዝ ምክንያት ከሚሆን በኅብረት በመሥራት ሁሉም በአንድነት እንዲበለጽግ ለማድረግ የሚያስችለውን የመሬት ይዞታ መሠረት በመጣል በመሆኑ ፤

መሳፍንቱና መኳንንቱ እንዲሁም ሌሎች በቂ መተዳደሪያ ያላቸው ጥቂት ሰዎች ሁሉ በሌሎች ወዝና ልፋት እንጊበለጽጉ ያቋቋሙትን ባላባታዊ ሥርዓት ለመደምሰስና የገጠሩን የልማት ምንጮች ከዚህ ሥርዓት በማላቀቅ ፤ ያገሪቱን የእርሻ ምርት ከፍ ለማድረግና አራሹ የድካሙ ፍሬ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ ለመመሥረት ፤

PROCLAMATION No. 31 OF 1975

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PUBLIC OWNERSHIP OF RURAL LANDS

"ETHIOPIA TIKDEM"

WHEREAS, in countries like Ethiopia where the economy is agricultural a person's right, honour, status and standard of living is determined by his relation to the land;

WHEREAS, several thousand *gashas* of land have been grabbed from the masses by an insignificant number of feudal lords and their families as a result of which the Ethiopian masses have been forced to live under conditions of serfdom;

WHEREAS, it is essential to fundamentally alter the existing agrarian relations so that the Ethiopian peasant masses which have paid so much in sweat as in blood to maintain an extravagant feudal class may be liberated from age-old feudal oppression, injustice, poverty, and disease, and in order to lay the basis upon which all Ethiopians may henceforth live in equality, freedom, and fraternity;

WHEREAS, the development of Ethiopia of the future can be assured not by permitting the exploitation of the many by the few as is now the case, but only by instituting basic change in agrarian relations which would lay the basis upon which, through work by cooperation, the development of one becomes the development of all;

WHEREAS, in order to increase agricultural production and to make the tiller the owner of the fruits of his labour, it is necessary to release the productive forces of the rural economy by liquidating the feudal system under which the nobility, aristocracy and a small number of other persons with adequate means of livelihood have prospered by the toil and sweat of the masses;

WHEREAS, it is necessary to provide work for all rural people;

ለገጠሬው ሕዝብ በሙሉ ሥራ ለመስጠት ፤

መሬት በመደልደል የገጠሬውን ሕዝብ ገቢ ከፍ በማድረግ የኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት ለመጣልና የገጠሩ ሕዝብ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ለመግዛት እንዲችል በማድረግ ጠቅላላውን የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት ለማሳደግ ፤

የባላባታዊውን ሥርዓት በመደምሰስ ያላግባብ በዚህ ሥርዓት የተዋጠውን የሰው ጉልበት ለኢንዱስትሪ እንዲቀርብ ለማድረግ ፤

በገጠሬው ሕዝብ መካከል ያለውን ያልተመጣጠነ ሀብትና ገቢ ለማደላደል ፤

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀ መንበሩን ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቍጥር ፪/፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በአንቀጽ ፮ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል ።

ምዕራፍ ፩
መግቢያ ፤

፩ ፤ አጭር ርእስ ፤

ይህ አዋጅ «የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቍጥር ፴፩/፲፱፻፷፯ ዓ.ም.» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪ ፤ ትርጓሜ ፤

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጕም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

፩/ «የገጠር መሬት» ማለት ከማዘጋጃ ቤት ወይም ከከተማ ክልል ውጪ የሚገኝ ማንኛውም መሬት ነው ፤

፪/ « ሰፊ እርሻ » ማለት በዘመናዊ ዘዴ የሚካሔድ የከብት ርቢ ሥራ ወይም በመኪናዎች የሚታረስ እርሻ ነው ።

፫/ « ጭሰኛ» ማለት መሬት ከባለርስት ወይም መሬቱን ለማከራየት መብት ካለው ሰው ተከራይቶ በግል የሚያርስ ነው ።

፬/ « የመንግሥት እርሻ » ማለት ባለሀብትነቱና አስተዳደሩ የመንግሥት የሆነ እርሻ ነው ።

፭/ « የኅብረት እርሻ » ማለት ይዞታውና አስተዳደሩ በመሬቱ የሚጠቀሙት ገበሬዎች የሆነ እርሻ ነው ።

፮/ « ድርጅት » ማለት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቍጥር ፫፻፺፰ የተመለከተው ወይም በዚሁ ሕግ ቍጥር ፬፻፬ ወይም ፬፻፯ ትርጓሜ ሥር የሚመጣ ማናቸውም ማኅበር ነው።

፯/ « ቋሚ ንብረት » ማለት እንደመስኖ ሥራዎች ፤ የውሃ ጕድጓዶች ፤ ቤቶችና ከድንጋይ ፤ ከሲሚንቶ ፤ ከሸክላ ፤ ከብረታ ብረት ወይም የተጠቀሱትን በማደባለቅ የተቋቋመ ሌላ ሥራ ነው ።

፰/ « የንግድ ማኅበር » ማለት ማንኛውም በንግድ ሕግ መጽሐፍ ፪ የተገለጠው የንግድ ማኅበር ነው ።

፱/ « አትክልት » የሚለው ቃል እንደ ቡና ዛፍ ፤ ጌሾ ዛፍ ፤ ባሕር ዛፍ ፤ እንሰት ተክል ፤ ጫት ተክል የመሳሰሉትንና የፍራፍሬ ተክሎችንም ያጠቃልላል ።

፲/ «ሚኒስትር» ማለት ሌላ መግለጫ ካልተሰጠው በስተቀር የመሬት ይዞታ ማሻሻያና አስተዳደር ሚኒስትር ነው ።

ምዕራፍ ፪
የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ስለማድረግ

፫ ፤ የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ስለማድረግ ፤

፩/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የገጠር መሬት በሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት ሆኗል ።

WHEREAS, it is necessary to distribute land, inc income, and thereby lay the basis for the expansion o and the growth of the economy by providing for the pa of the peasantry in the national market;

WHEREAS, it is essential to abolish the feudal order to release for industry the human labour suppres such system;

WHEREAS, it is necessary to narrow the gap in ru and income;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article Definition of Powers of the Provisional Military Adm Council and its Chairman Proclamation No. 2/1974, i proclaimed as follows:

CHAPTER 1
INTRODUCTION

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Public O of Rural Lands Proclamation No. 31/1975"

2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context otherwise

1) "rural land" shall mean all land outside the b of a municipality or a town.

2) "large-scale farm" shall mean mechanized far dern animal husbandry.

3) "tenant" shall mean any person who persona vates land rented from a landowner or from a who has a right to lease such land.

4) "State farm" shall mean any farm owned and stered by the State.

5) "co-operative farm" shall mean any farm the sion and administration of which belong to using the land.

6) "organization" shall mean the body referred t ticle 398 of the Civil Code or any association w under Article 404 or 407 of the same Code.

7) "permanent works" shall mean irrigation work wells, buildings and other works made out o concrete, bricks, metal, or any combination t

8) "business organization" shall mean any orga provided for in Book II of the Commercial Co

9) "tree-crops" shall include such trees and plant fee and eucalyptus, *chatt*, *enset* and hops, as fruit trees.

10) "Minister" shall mean, unless otherwise indica Minister of Land Reform and Administration.

CHAPTER 2
Public Ownership of Rural Lands

3. *Public Ownership of Rural Lands*

1) As of the effective date of this Proclamation, lands shall be the collective property of the E people.

፪/ ማንኛውም ሰው ወይም የንግድ ማኅበር ወይም ሌላ ድርጅት የገጠር መሬትን በግል ባለሀብትነት ለመ ያዝ አይችልም ።

፫/ የገጠር መሬትንና በላዩ ላይ የሚገኙትን ደኖችና አት ክልቶች በሚመለከት ረገድ ካሣ አይከፈልም ። ሆኖም በመሬቱ ላይ ለሚገኙ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ተገቢው ካሣ ይከፈላል ።

፬ ፤ የግል ባለሀብትነት ሥሪት ባላቸው ክፍላተ ሀገር የገጠር መሬት ለአራሹ በይዞታ ስለመሰጠቱ ፤

፩/ ጾታ ሳይለይ ማንኛውም ለማረስ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ ኑሮ በቂ የሆነ የገጠር መሬት በይ ዞታ ያገኛል ።

፪/ ማንኛውም ባለርስት የነበረ ሰው ለማረስ ፈቃደኛ ከሆነ እንደሌላው ትራሽ መሬት የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው ።

፫/ የአንድ አራሽ ቤተሰብ በማናቸውም ጊዜ በይዞታ የሚያገኘው መሬት ከ፲ ሄክታር (ሩብ ጋሻ) አይበ ልጥም ።

፬/ በተቻለ መጠን አ/ ሾች የሚያገኙት መሬት እኩል ይሆናል ፤ ሆኖም እንደአካባቢው ሁኔታና እንደመ ሬቱ ለምነት የይዞታው መጠን ሊለያይ ይችላል ።

፭/ ማንኛውም ፡ ፡ሽ ሌላ ሰው በመቅጠር ለማሳረስ አይ ችልም ። ሆነ ሌላ በቂ መተዳደሪያ የሌላት ሴት ወይም ባለይዞታ ሲሞት ፤ ሲታመም ወይም ሲያረጅ ሚስቱ ወይም ባልየው ወይም አካለ መጠን ያላደረሱ ልጆቹ ሠራተኛ በመቅጠር ለማሳረስ ይችላሉ ።

፮/ ሚኒስትሩ ለአንድ ቤተሰብ ኑሮ በቂ የሚሆነውን የይ ዞታ መጠን በደንብ ይወስናል ።

፭ ፤ መሬት ማስተላለፍ ስለመከልከሉ ፤

ማናቸውም ሰው በይዞታ ያገኘውን መሬት የመሸጥ ፤ የመለወጥ ፤ የማውረስ ፤ የማስያዝ ፤ በወለድ አግድ የመ ስጠት ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብት አይ ኖረውም ። ሆኖም ባለይዞታው ሲሞት ፤ የሟች ሚስት ወይም ባል ወይም አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ ወይም እነዚህ ከሌሉ አካለ መጠን ያደረሰ ልጅ በይዞታው ተተ ክቶ የመጠቀም መብት ይኖረዋል ።

፮ ፤ ስለ ጭሰኞች ይዞታ ፤

፩/ በዚህ አዋጅ በምዕራፍ ፫ መሠረት በገበሬዎች ማኅ በር መሬት እስኪደላደል ድረስ ማንኛውም ጭሰኛ ወይም የቅጥር ገበሬ በሚያርሰው መሬት ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል ። ሆኖም በመሬቱ ላይ የሚኖር የእጅ አራሽ የሌለው ባለርስት በመሬቱ ላይ ካሉት ጭሰኞች ጋር መሬቱን እኩል የመካፈል መብት ይኖ ረዋል ። ይህንንም የባለርስት መብት መንግሥት ተገቢ በመሰለው መንገድ ያስከብራል ።

ሌላ በቂ መተዳደሪያ ከሌላት ሴት ወይም በሕመም ወይም በእርጅና ወይም በዕድሜ ማነስ ምክንያት በግል ለማረስ ከማይችሉ ሰዎች የተከራየ ጭሰኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው መብት ሊቀጠም አይችልም ።

2) No person or business organization or any other organization shall hold rural land in private ownership.

3) No compensation shall be paid in respect of rural lands and any forests and tree-crops thereon; provided that fair compensation shall be paid for movable properties and permanent works on the land.

4. *Distribution of Land to the Tiller in Provinces with privately Owned Rural Lands*

1) Without differentiation of the sexes, any person who is willing to personally cultivate land shall be allotted rural land sufficient for his maintenance and that of his family.

2) Any person who has been a landowner and is willing to personally cultivate land shall likewise be allotted land.

3) The size of land to be allotted to any farming family shall at no time exceed 10 hectares (¼ of a gasha).

4) The size of land to be allotted to farming families shall as far as possible be equal; provided that it may vary depending on the local conditions and the productive potential of the land.

5) No person may use hired labour to cultivate his holding; provided that the foregoing prohibition shall not apply to a woman with no other adequate means of livelihood, or where the holder dies, is sick or old, to the wife or the husband or to his or her children who have not attained majority.

6) The Minister shall determine by regulations the size of land sufficient for the maintenance of a farming family.

5. *Prohibition of Transfer of Land*

No person may by sale, exchange, succession, mortgage, antichresis, lease or otherwise transfer his holding to another; provided that upon the death of the holder the wife or husband or minor children of the deceased or where these are not present, any child of the deceased who has attained majority, shall have the right to use the land.

6. *Tenant's Holding*

1) Until all lands are distributed pursuant to Chapter 3 of this Proclamation, any tenant or hired laborer shall have possessory right over the land he tills; provided that a resident landowner who has leased out all his lands shall have the right to equally share the land with his tenants. The Government shall protect the rights of such landowner in any way it thinks fit.

2) The provisions of the preceding sub-article shall not apply to a person who has rented land from a woman with no other adequate means of livelihood or from a person who by reason of illness, old age or youth, cannot personally cultivate his holding.

፫/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በባለርስትና በጭሰኛ መካከል የነበረው ግንኙነት ፈርሷል ። ስለዚህ ጭሰኛው ከሁን በፊት ለባለርስት ሲሰጥ ከነበረው ኪራይ ፣ ሌላ ክፍያ ፣ ማንኛውም አገልግሎትና ዕዳ ነፃ ሆኗል ፣ እንዲሁም መሬቱን ለጭሰኛው በወለድ አግድ ያስያዘ ባለርስት ከዕዳ ነፃ ሆኗል ።

፬/ ጭሰኛው ይጠቀምበት የነበረውን የባለርስት የእርሻ መሣሪያና ከአንድ ጥንድ የማይበልጥ በሬ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ግምት በመክፈል የማስቀረት መብት አለው ። ሆኖም ሌላ የእርሻ መሣሪያ ፣ በሬ ወይም በቂ መተዳደሪያ የሌለው ባለርስት ለጭሰኛ የሰጠውን የእርሻ መሣሪያና በሬ መልሶ ለመውሰድ ይችላል ።

፯ ፣ ስለ ሰፊ እርሻዎች ፣

፩/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ማንኛውም ሰፊ እርሻ እንደየሁኔታው የመንግሥት ወይም የኅብረት እርሻ ይሆናል ፣ ወይም ተከፋፍሎ ለአራሾች ይሰጣል። ሆኖም የመንግሥት ወይም የኅብረት እርሻ እስኪቋቋም ድረስ ሰፊውን እርሻ መንግሥት ተገቢ መስሎ በሚታየው መንገድ ያስተዳድራል ። መንግሥት ተገቢ በመሰለው መንገድ ለማስተዳደር እስኪወስን ድረስ እነዚህን እርሻዎች ባለሀብቶቹ የነበሩት ያስተዳድራሉ ።

፪/ በሰፊ እርሻዎች ላይ ለሚገኙት ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች መንግሥት ተገቢውን ግምት ይከፍላል ። ሆኖም ግምቱ የመሬቱን ዋጋ አይጨምርም ።

ምዕራፍ ፫

አዋጁን በሥራ ላይ ለማዋል የሚቋቋሙት ማኅበሮች

፰ ፣ የገበሬዎች ማኅበር ስለማቋቋም ፣

አዋጁን ለማስፈጸም ለልማት በሚያመች መንገድ ያንድ ጭቃን ክልል መሠረት በማድረግ ከ፰፻ ሄክታር (፳ ጋሻ) በማያንስ ክልል ውስጥ የገበሬዎች ማኅበር ይቋቋማል ።

፱ ፣ የገበሬዎች ማኅበር አባሎች ፣

፩/ የገበሬዎች ማኅበር አባል ለመሆን የሚችለው ፣ ጭሰኛ የነበረ ፣ መሬትና መተዳደሪያ የሌለው ፣ ተቀጥሮ የሚሠራ የእርሻ ሠራተኛና ከ፲ ሄክታር (ሩብ ጋሻ) ያልበለጠ መሬት ባለርስት የነበረ ሰው ነው።

፪/ በአንቀጽ ፲ (፩) መሠረት የመሬት ማደላደል ተግባር ከተፈጸመ በኋላ ማንኛውም ባለርስት የነበረ ሰው የገበሬዎች ማኅበር አባል ለመሆን ይችላል ።

፲ ፣ የገበሬዎች ማኅበር ተግባር ፣

የገበሬዎች ማኅበር ተግባር የሚከተለው ይሆናል ፦

፩/ በአንቀጽ ፰ በተጠቀሰው ክልል ውስጥ ያለውን መሬት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንግሥት ርዳታ እየጠየቀ በተቻለ መጠን በእኩልነት በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት ማደላደል ፣

ሀ/ በክልሉ ውስጥ በአራሽነት ለቆዩ ጭሰኞችና በክልሉ ውስጥ ባለርስቶች ለነበሩ ፣

ለ/ ከክልሉ ተባርረው ለነበሩ ጭሰኞች ፣

ሐ/ በክልሉ ውስጥ ኗሪ ሆነው በቂ ሥራና መተዳደሪያ ላልነበራቸው ሰዎች ፣

3) As of the effective date of this proclamation th[e rela]tionship between landowner and tenant is abol[ished]. Accordingly, the tenant shall be free from paym[ent to] the landowner of rent, debts or any other oblig[ations]. Likewise, a landowner who has given his land i[n anti]chresis to a tenant shall be free from the paym[ent of] his debt.

4) The tenant shall have the right to retain agric[ultural] implements and a pair of farm oxen belonging [to the] landowner for which a reasonable compensation [shall] be paid to the landowner within a period not exc[eeding] three years; provided that a landowner with [no] agricultural implements and farm oxen or no ad[equate] means of livelihood may take back his implemen[ts and] oxen from the tenant.

7. *Large-Scale Farms*

1) As of the effective date of this proclamation, any l[arge] scale farm shall be organized as a State or [co]operative farm or shall be allotted to tillers; pro[vided] that until the establishment of State or co-ope[rative] farms the Government shall administer such f[arms] in any manner it deems fit and provided further [that] until the Government decides upon the manner in w[hich] such farms are to be administered, the ex-owne[rs of] these farms shall have the responsibility to con[tinue] administering them.

2) The Government shall pay fair compensation for [mov]able property and permanent works on such l[and]; provided that compensation shall not be paid for [the] value of the land.

CHAPTER 3

Establishment of Associations for the Implementation of the Proclamation

8. *Establishment of Peasant Associations*

To carry out the provisions of this proclamation a pea[sant] association shall be formed, in a manner suitable for de[ve]lopment purposes, taking a *chika* area as a basis, with [a] minimum area of 800 hectares (20 gashas).

9. *Members of the Association*

1) A tenant, a landless person, a hired agricultural wo[rker] or a landowner with less than 10 hectares of land [may] become a member of the Association.

2) After completion of the distribution of land pursu[ant] to Article 10 (1) hereof, any person who had bee[n a] landowner may become a member of the Associatio[n].

10. *Functions of Peasant Associations*

The functions of peasant associations shall be the follow[ing]:

1) to distribute, with the solicited assistance of the Gov[ern]ment when necessary, land forming the area mentio[ned] in Article 8 as much as possible equally, and in [the] following order:

a) to farmer tenants and former landowners within the area,

b) to evicted tenants;

c) to persons who reside within the area [who do not] have work or sufficient means of livelih[ood];

መ/ ከክልሉ ውጪ ለሚመጡ ገበሬዎች ፤

ሠ/ ጡረታ ለወጣና መሬቱን ራሱ ለማረስ ለሚችል ሰው ፤

ረ/ ለመተዳደሪያ መሬት ለሚያስፈልጋቸው ድርጅቶች ፤

፪/ ስለ መሬት አጠቃቀም መንግሥት ሚሰጠውን መመሪያ መከተል ፤

፫/ በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም የሕዝብ ንብረት መጠበቅና ማስተዳደር ፤ በተለይም የአፈር የውሃና የደን ሀብትን መጠበቅና መቆጣጠር ፤

፬/ በክልሉ ውስጥ የሚነሣውን የመሬት ክርክር ለማየት የፍርድ ሸንጐ ማቋቋም፤

፭/ የገበያና የብድር እንዲሁም በአራሾች መካከል የጉልበትም ሆነ ሌላ እንደ ደቦ የመሳሰሉ የመረዳጃ ንዑስ ማኅበሮች ማቋቋም ፤

፮/ ከመንግሥት ጋር በመተባበር ለክልሉ የሚያስፈልጉትን የትምህርት ፤ የጤናና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ማቋቋም ፤

፯/ በሕመም ፤ በእርጅና ፤ በዕድሜ ማነስ ፤ ወይም ባልየው በመሞቱ ምክንያት ለማረስ ለማይችሉ ሰዎች ይዞታቸው እንዲታረስ ማድረግ ፤

፰/ በአንድነት የሚኖሩበትና የሚሰበሰቡበት መንደር እንዲፈጠር ማድረግ ፤

፱/ የማዕድንና የደን መሬት እንዲሁም የታሪካዊና ጥንታዊ ቅርስ ቦታዎች እንዳይደለደሉ ማድረግ ፤

፲፩ ፤ በከፍተኛ ደረጃ ስለ ሚቋቋመው የገበሬዎች ማኅበር ፤

፩/ የእያንዳንዱ ክልል የገበሬዎች ማኅበር ተወካዮች የሚገኙበት ማኅበር በየወረዳው ይቋቋማል ።

፪/ የወረዳ ገበሬዎች ማኅበር ፤

ሀ/ በአንቀጽ ፲ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፤ (፪) ፤ (፫) ፤ (፭) ፤ (፮) (፯) ፤ (፰) እና (፱) የተጠቀሱትን የገበሬዎች ማኅበር ተግባሮች ያስተባብራል ፤

ለ/ በወረዳ ክልል ውስጥ የሚገኙት ገበሬዎች በተቻለ መጠን እኩልና የተመጣጠነ ይዞታ እንዲኖራቸው ለማድረግ በክልሎች መካከል ይዞታን የማሸጋሸግ ሥልጣን ይኖረዋል ፤

ሐ/ ማንኛውም መሬትና መተዳደሪያ የሌለው ሰው መሬት እንዲሰጠው ሲያመለክት መሬት ካለው ክልል መሬት ፈልጐ ይሰጣል ፤

መ/ በክልል ደረጃ የታዩትን የመሬት ክርክሮች በይግባኝ ደረጃ የሚወስንና በክልሎች መካከል የሚነሳውን የመሬት ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሚያይ የወረዳ የፍርድ ሸንጎ ያቋቁማል ። የወረዳው የፍርድ ሸንጎ በይግባኝ ደረጃ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

፫/ የእያንዳንዱ ወረዳ ገበሬዎች ማኅበር ተወካዮች የሚገኙበት ማኅበር በየአውራጃው ይቋቋማል ።

፬/ የአውራጃ ገበሬዎች ማኅበር ፤

ሀ/ የወረዳ ገበሬዎች ማኅበር ተግባርን ያስተባብራል፤

ለ/ በወረዳ ገበሬዎች ማኅበር የፍርድ ሸንጎ በመጀመሪያ ደረጃ የተወሰኑትን የመሬት ክርክሮች በይግባኝ ደረጃ የሚወስን የአውራጃ የፍርድ ሸንጎ ያቋቁማል ። የአውራጃው የፍርድ ሸንጎ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

d) to farmers coming from outside of the area,

e) to pensioned persons who are willing to undertake personal cultivation,

f) to organizations needing land for their upkeep.

2) to follow land-use directives to be issued by the Government;

3) to administer and conserve any public property within the area especially the soil, water and forest;

4) to establish judicial tribunals to hear land disputes arising within the area;

5) to establish marketing and credit co-operatives and other associations like the *debo* which would help farmers to co-operate in manual and other works;

6) to build with the co-operation of the Government schools, clinics and similar institutions necessary for the area;

7) to cultivate the holdings of persons who, by reason of old age, youth or illness, or in the case of a woman, by reason of her husband's death, cannot cultivate their holdings;

8) to undertake villagization programmes;

9) to exclude from distribution mining and forest lands and places of historical and antiquarian significance.

11. *Peasant Associations Established at Higher Levels*

1) There shall be established a Woreda peasant association composed of delegates from each association established at an area level.

2) The Woreda peasant association shall:

a) co-ordinate the functions of the peasant association provided for under Article 10, sub-articles 1, 2, 3, 5, 6, 7, 8 and 9,

b) have the power to change the boundaries of areas so that peasants within a Woreda shall have, as far as possible, equal holdings,

c) upon request allot land from an area which has unoccupied land to any person who has no land or other means of livelihood,

d) establish a Woreda judicial tribunal which shall hear and decide appeals from the decision of the judicial tribunal at the area level, and which shall have first instance jurisdiction to hear land disputes arising between areas; appellate decisions given by the Woreda judicial tribunal shall be final.

3) There shall be established an Awraja peasant association composed of delegates from each Woreda peasant association.

4) The Awraja peasant association shall:

a) co-ordinate the functions of the Woreda peasant associations;

b) establish an Awraja judicial tribunal which shall hear land disputes decided at first instance by the Woreda judicial tribunal. Decisions given by the Awraja judicial tribunal shall be final.

ምዕራፍ ፬

የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር ፣

፲፪ ፣ የገበሬዎች ማኅበር ስለማቋቋም ፣

፩/ ሚኒስትሩ ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በዚህ አዋጅ መሠረት የገበሬዎች ማኅበር በየደረጃው እንዲቋቋም ያደርጋል ።

፪/ ሚኒስትሩ የገበሬዎች ማኅበርን በምክርና በሌላም ልዩ ልዩ መንገድ ፣ሚረዳ ቢያንስ በየወረዳው አንዳንድ የመሬት ይዞታ ወኪል ይመድባል ።

፫/ የመሬት ይዞታው ወኪል ገበሬዎችን በመሰብሰብና የአዋጁን መንፈስና ዓላማ በመግለጥ ማኅበሩ እንዲቋቋም ያደርጋል ።

፲፫ ፣ አዋጁን ለሕዝብ በይፋ ስለማሳወቅ ፣

፩/ ሚኒስትሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና ዓላማ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ለሕዝቡ ማሳወቅ ፣ መግለጥና ማስረዳት አለበት ።

፪/ በተለይም ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ወዲያውኑ በባለርስትና ጭሰኛ መካከል ያለው ግንኙነት መቋረጡንና የገበሬዎች ማኅበር በተቻለ ፍጥነት እንዲቋቋም ማስፈለጉን ለሕዝብ በይፋ መግለጥ አለበት ።

፲፬ ፣ የመሬት ክርክር የማየት ሥልጣን ፣

፩/ የመሬት ይዞታ ወኪል በወረዳና በአውራጃ ደረጃ ለሚቋቋመው የገበሬዎች ማኅበር የፍርድ ሸንጎ አባል ሆኖ በሊቀ መንበርነት ያገለግላል ። ሆኖም ማንኛውም ወኪል በወረዳ ደረጃ በመጀመሪያ ደረጃ ያየውን ክርክር መልሶ በአውራጃ ደረጃ ለማየት አይችልም።

፪/ የመሬት ይዞታ ወኪል የፍርድ ሸንጎ ጽሕፈት ቤት አቋቁሞ በተለይም በመዝገብ አያያዝ ረገድ ያለውን ሥራ በበላይነት ይመራል ።

፲፭ ፣ መዝገብ ስለማቋቋም ፣

፩/ ሚኒስትሩ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሎች ፣ በወረዳዎችና በአውራጃዎች የሚገኙትን የገበሬዎች ስም ዝርዝር የያዘ መዝገብ በየደረጃው ያቋቁማል ።

፪/ ሚኒስትሩ የክልሎችን ወሰን ለመለየትና ሌላም ከዚህ ጋር የተያያዘ አስፈላጊ ተግባር ለማከናወን ቀያሾች ይመድባል ።

፲፮ ፣ ሰፊ እርሻዎችን የመንግሥት ወይም የኅብረት ስለማድረግ

፩/ ሚኒስትሩ ሰፊ እርሻዎችን እንደየሁኔታው የመንግሥት ወይም የኅብረት እርሻ እንዲሆኑ ወይም እንዲከፋፈሉ ያደርጋል ።

፪/ ሚኒስትሩ በሰፊ እርሻዎች ላይ ለሚገኘው ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት የሚከፈለውን ካሣ መጠን ይወስናል ።

፲፯ ፣ መሬት ለመንግሥት አገልግሎት ስለመውሰድ ፣

፩/ መንግሥት ለትምህርት ቤት ፣ ለሆስፒታል ፣ ለመንገድ ፣ ለመሥሪያ ቤት ፣ ለእርሻ ጣቢያ ፣ ለጦር ሠፈርና ለመሳሰሉት የሕዝብ አገልግሎቶች ሲባል በገበሬዎች ማኅበር ይዞታ ለመጠቀም ይችላል ።

፪/ መንግሥት በገበሬዎች ማኅበር ይዞታ በመጠቀሙ ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት አስፈላጊውን ግብተካከያ ያደርጋል ።

CHAPTER 4

Powers and Functions of the Minister of Land Reform and Administration

12. *Establishment of Peasant Associations*

1) The Minister shall, with the co-operation of the M of Interior, help in the formation of peasant asso at every level in accordance with the provisions Proclamation.

2) The Minister shall assign at least one Land Officer to every Woreda. The functions of the shall be to give advice to peasant associations a them in any other manner.

3) The Land Reform Officer shall help in the for of peasant associations by calling assemblies o sants and explaining the purposes and intentions Proclamation.

13. *Publicizing of the Proclamation*

1) The Minister shall notify and explain to the pub provisions and aims of this Proclamation throu mass media.

2) In particular the Minister shall notify the public termination of tenancy relationships after the e date of this Proclamation and of the necessity of peasant associations as soon as possible.

14. *Power to Hear Land Disputes*

1) The Land Reform Officer shall act as chairman judicial tribunal of the peasant association esta at Woreda and Awraja levels; provided that no Reform Officer who has presided over a case Woreda level may do the same at Awraja level

2) The Land Reform Officer shall establish the o the judicial tribunal and shall in particular be in of keeping records of the office.

15. *Establishment of Registers*

1) The Minister shall establish such registers as n necessary containing the names of peasants a area, Woreda and Awraja level.

2) The Minister shall assign surveyors to help in t marcation of areas and in any other related acti

16. *Organizing Large-scale Farms into State or Co-op Farms*

1) The Minister shall determine which large-scale may be State or co-operative farms or which distributed to tillers.

2) The Minister shall determine the compensation paid in respect of permanent works and movab perties on the large-scale farms.

17. *Power of Expropriation*

1) The Government may use land belonging to associations for public purposes such as schools, tals, roads, offices, military bases and agricultur jects.

2) The Government shall make good such damag may cause to the peasant association by the deci expropriate the holding.

፲፰. ሕዝብ ስለማስፈር ፤

በዚህ አዋጅ መሠረት መሬት በሚደለደልበት ጊዜ መሬት በማነሱ ምክንያት ያለመሬት ለሚቀሩ ወይም ይዞታቸው እጅግ አነስተኛ ለሆነ አራሾች መንግሥት የማስፈር ወይም በቀበሌው የጎጆ እንዱስትሪዎች የማ ቋቋም አላፊነት ይኖርበታል ።

ምዕራፍ ፭

ስለ ወል ርስትና የዘላን መሬቶች

፲፱. ስለ ወል ርስት ፤

በወል ርስት ወይም በቀበሌ ባለሀብትነት በተያዙ መሬቶች ላይ የሚገኙ አራሾች ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሚያርሱት መሬት ላይ የይዞታ መብት ይኖራ ቸዋል ።

፳. መሬት ስለሚጠይቁ ተወላጆች ፤

በወል ርስት ወይም በቀበሌ ባለሀብትነት ከተያዙ መሬቶች ላይ ማንኛውም ተወላጅ በአዲስ ጠያቂነት መሬት ሊካፈል አይችልም ።

፳፩. ለድርጅቶችና ለግለሰቦች ስለሚደረገው ክፍያ ፤

በወል ርስት ወይም በቀበሌ ባለሀብትነት በተያዙ መሬቶች ላይ የሚኖረው አራሽ ለአንዳንድ ድርጅቶች ጭቃ ሹሞች ፣ ጉልተ ገገሮች ፣ ፈረሰኞችና ለመሳሰ ሉት የሚከፍለው ማንኛውም ዓይነት ክፍያ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ቀሪ ሆኗል ።

፳፪. በወል ርስት ስለሚገኙ ጭሰኞች ፤

፩/ በወል ርስት ወይም በቀበሌ ባለሀብትነት በተያዙ መሬቶች ላይ በጭሰኝነት የሚያርስ መሬት የሌለው አራሽ በሚያርሰው መሬት ላይ የይዞታ መብት ይኖ ረዋል ። ሆኖም ሌላ በቂ መተዳደሪያ ከሌላት ሴት ወይም በሕመም ወይም በእርጅና ወይም በዕድሜ ማነስ ምክንያት በግል ለማረስ ከማይችሉ ሰዎች የተ ከራየ ጭሰኛ በዚህ መብት ሊጠቀም አይችልም ።

፪/ በወል ርስት ወይም በቀበሌ ባለሀብትነት በተያዙ መሬቶች ላይ በጭሰኝነት የሚያርስ ፣ የራሱ መሬት ያለው አራሽ በጭሰኝነት በሚያርሰው መሬት ላይ የይዞታ መብት አይኖረውም ።

፫/ በመሬቱ ላይ የሚኖር የእጅ እራሽ የሌለውና መሬ ቱን ያከራየ ሰው በመሬቱ ላይ ካሉት ጭሰኞች ጋር መሬቱን እኩል የመካፈል መብት ይኖረዋል ።

፳፫. በወል ርስት የገበሬዎች ማኅበር ስለማቋቋም ፤

በወል ርስት ወይም በቀበሌ ባለሀብትነት በተያዙ መሬቶች ለልማት በሚያመች መንገድ የአንድ ደብርን ወይም ጎጥን ክልል መሠረት በማድረግ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ ፫ መሠረት የገበሬዎች ማኅበር ይቋቋማል ። የገበሬዎች ማኅበርም ዋና ተግባር መሬት በኅብረት እን ዲታረስ ገበሬዎችን ማነቃቃትና ማደራጀት ይሆናል ። እንዲሁም በአንቀጽ ፲ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፱) የተመለከቱትን ተግባሮች ያከናውናል ።

፳፬. ስለ ዘላን መሬቶች ፤

የዘላን ሕዝቦች ለግጦሽ ወይም ከእርሻ ጋር ለተያያዘ ተግባር በባህላቸው መሠረት በሚጠቀሙበት መሬት ላይ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የይዞታ መብት ይኖ ራቸዋል ። ስለሆነም በኢንተርናሽናል ደረጃ የዘላን መሬት የሚነኩ ስምምነቶች የተጠበቁ ናቸው ።

18. *Settlement*

The Government shall have responsibility to settle peasants or to establish cottage industries to accommodate those who, as a result of the distribution of land in accordance with the provisions of this proclamation, remain with little or no land.

CHAPTER 5

Communal and Nomadic Lands

19. *Communal Lands*

As of the effective date of this Proclamation, peasants in *Rist* or *Deissa* areas shall have possessory rights over the lands they presently till.

20. *New Claimants*

As of the effective date of this Proclamation, no person may put claims to land in *Rist* or *Deissa* areas.

21. *Payment to Organizations and Individuals*

As of the effective date of this Proclamation, all obligations of the peasantry in *Rist* or *Deissa* areas to pay dues to any organization, *chika shum, gultegna, feressegna*, and the like are hereby annulled.

22. *Tenants in Rist or Deissa Areas*

1) Landless tenants in *Rist* or *Deissa* areas shall have possessory rights over the land they till; provided that the foregoing shall not apply to tenants who have rented the land from a woman with no other adequate means of livelihood or from persons who, due to illness, old age or youth, cannot personally cultivate their holdings.

2) Tenants who have land of their own shall not have possessory rights over the land they cultivate as tenants.

3) A resident landowner who has leased out all his land to tenants shall have the right to equally share the land with his tenants.

23. *Peasant Associations in Areas of Communal Ownership*

In *Rist* or *Deissa* areas peasant associations shall, pursuant to Chapter 3 of this Proclamation, be established in a manner suitable for development purposes taking a *debr* or *got* as a basis. The main function of the peasant association shall be to induce and organize peasants into co-operative farms. It shall also carry out the functions enumerated in Article 10 (2) to (9) hereof.

24. *Nomadic Lands*

As of the effective date of this Proclamation, nomadic people shall have possessory rights over the lands they customarily use for grazing or other purposes related to agriculture. Nothing in the foregoing shall affect international agreements relating to nomadic lands.

፳፭ ፤ የዘላን ሕዝቦች ስለሚያደርጉት ክፍያ ፤

የዘላን ሕዝቦች ለባላባት ወይም ለማንኛውም ሌላ ሰው የሚያደርጉት ክፍያ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ቀሪ ሆኗል ።

፳፮ ፤ ማኅበር ስለማቋቋም ፤

የዘላን ሕዝቦች አዋጁን ለማስፈጸም ለልማት በሚያመች መንገድ ማኅበር ያቋቁማሉ ። የማኅበሩም ዋና ተግባር አባሎቹ በግጦሽ አያያዝና በውሀ አጠቃቀም እንዲተባበሩ ማድረግ ይሆናል ። እንዲሁም በአንቀጽ ፲ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፱) የተመለከቱትን ተግባሮች ያከናውናል ።

፳፯ ፤ መንግሥት ስለሚያደርገው ርዳታ ፤

መንግሥት የዘላን ሕዝቦች የግጦሽ መሬት የማሻሻል የውሀ ጉድጓዶች የመቆፈርና በይዞታቸው ላይ ለእርሻ የማስፈር አላፊነት ይኖርበታል ።

ምዕራፍ ፮

ጠቅላላ ውሳኔዎች ፤

፳፰ ፤ ክስ ስለማገድ ፤

፩/ ይህ አዋጅ በጸናበት ቀን በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚገኙ የገጠርን መሬት የሚመለከቱ ክርክሮች በሙሉ ተሰርዘዋል ።

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የገበሬዎች ማኅበር የፍርድ ሸንጎ እስኪቋቋም ድረስ በማንኛውም መደበኛ ፍርድ ቤት የገጠር መሬት ክስ ሊቀርብ አይችልም ።

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት የገበሬዎች ማኅበር የፍርድ ሸንጎ ከተቋቋመ በኋላ ቢሆንም ማንኛውም ዓይነት የገጠር መሬት ክርክር ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች አይቀርብም ።

፬/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወሰደውን ርምጃ ሕጋዊነት ለመቃወም ማናቸውንም ክስ ለማቅረብ አይቻልም ።

፳፱ ፤ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ፤

ሚኒስትሩ የአዋጁን አንቀጾች ዓላማ በሚገባ ለማስፈጸም ደንቦችን ለማውጣት ይችላል ።

፴ ፤ ወ ን ጀ ሎ ች ፤

፩/ ይህን አዋጅ በሥራ ላይ እንዳይውል ያሰናከለ ወይም አዋጁን የጣሰ እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ በልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቊጥር ፴፭ መሠረት ይቀጣል ።

፪/ አዋጁን ለመቃወም ሲል ሰብል ፤ ደን ወይም ዛፍ ያቃጠለ ወይም የቆረጠ ወይም ቤት ፤ የእርሻ መሣሪያ ፤ የመስኖ ሥራ ፤ ወይም ግድብ ያፈረሰ ወይም ያበላሸ ወይም የእርሻ ከብት ያረደ ወይም የገደለ ማንኛውም ሰው እንደ ጥፋተኛ ተቆጥሮ በልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

፫/ በዚህ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን ያላግባብ የተጠቀመ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ በልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

25. *Payments made by Nomadic People*

As of the effective date of this Proclamation, all of the nomadic people to pay dues to *balabats* or persons are hereby annulled.

26. *Establishment of Associations*

Nomadic people shall form associations to effect out this Proclamation in a manner suitable for de purposes. The main function of the association induce the nomads to cooperate in the use of gr water rights. It shall also carry out the functions in Article 10 (2) to (9) hereof.

27. *Responsibility of the Government*

The Government shall have the responsibility to grazing areas, to dig wells and to settle the nomad for farming purposes.

CHAPTER 6

General Provisions

28. *Prohibition of Court Action*

1) All cases involving rural lands pending in the courts on the effective date of this Proclam hereby annulled.

2) No new case involving rural lands may be cr by any ordinary court until judicial tribunals of associations are established pursuant to the p of this Proclamation.

3) No cases involving rural lands may be brough any ordinary court even after the establishment cial tribunals of peasant associations pursuan provisions of this Proclamation.

4) No suit may be brought challenging the legality action taken pursuant to the provisions of this mation.

29. *Power to Issue Regulations*

The Minister may issue regulations to give effect to the poses and provisions of this Proclamation.

30. *Offences*

1) Any person who obstructs the execution of this mation or who violates the provisions of this mation shall be guilty of an offence and shall be able under Article 35 of the Special Penal Cod clamation.

2) Any person who, with the intention of violating the visions of this Proclamation, burns or cuts crops or trees or who destroys or damages houses, a tural implements, irrigation projects, dams or wh or kills livestock used for agricultural purpose be guilty of an offence and shall be punished und Special Penal Code Proclamation.

3) Any public servant who misuses the authority in him under the provisions of this Proclamation be guilty of an offence and shall be punishable the Special Penal Code Proclamation.

፴፩፤ የመግባት መብት ።

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የዚህ አዋጅ አንቀጾች የሚመለከቱትን ወይም ሊመለከቱት በሚችሉበት በማንኛውም መሬት ውስጥ ሥራውን ለማከናወን ለመግባት ይችላል ።

፴፪፤ ከሌሎች ሕጎች ጋር ስላለው ቅራኔ ፡

ማንኛውም ሕግ ፣ ደንብ ፣ የተለመደ አሠራር ወይም ሥነ ሥርዓት የተጻፈም ቢሆን ባይጻፍ በልማድ የሚሠራበት ሁሉ ይህን አዋጅ የሚቃረን ከሆነ ይህንን አዋጅ በሚመለከት ጉዳይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፴፫፤ አዋጁ ስለሚጸናበት ቀን ።

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

31. *Rights of Entry*

Any person authorised to perform any function under this Proclamation may, in exercising his duties, enter at any time any land which is or may come under the provisions of this Proclamation.

32. *Conflict with other Laws*

No law, regulation, practice or procedure, written or customary, shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation have force or effect in respect of situations provided for by this Proclamation.

33. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of March 4, 1975.

Done at Addis Ababa, this 29th day of April, 1975.

THE PROVISIONAL MILITARY ADMINISTRATION COUNCIL

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።
BERHANENA SELAM PRINTING PRESS

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።
BERHANENA SELAM PRINTING PRESS